# የሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለው ፡ ኃይልና ፡ ገደብ—

ከአርተር ፡ ቴይለር ፡ ቮን ፡ ሜኽረን ፤
ከሐርቫርድ ፡ ሕግ ፡ ት/ቤት ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. የኢትዮጵያን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ባወጁበት ፡ ጊዜ ፡ "ትክክለኛና ፡ ዝርዝር ፡ የሆኑ ፡ ደንቦች ፡" እንደሚያስፈልጉ ፡ በመቅድሙ ፡ ውስጥ ፡ ጠቅሰው ፡ በተጨማሪም ፡ "በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለኑሮው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መብቶቹንና ፡ ግዴታዎችን ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ እንዲገባው ፡ ለማድረግ ፡ ዐቅደን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ቃላቶች ፡ ግልጽ ፡ ሆነው ፡ እንዲዘጋጁ ፡ አድርገናል ። እንደዚሁም ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚመለከትና ፡ የሚጠቀልል ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ ያለውና ፡ የተሟላ ፡ እንዲሆን ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ ዛሬ ፡ በዐዋጅ ፡ የምናወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ይገኛል . . ." ብለዋል ።

ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የሚመለከተው ፡ የሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ መዋል ፡ በሚወሳበት ፡ ጊዜ ፡ በልማድ ፡ በአንክሮ ፡ የሚታዩትን ፡ በቀላሉ ፡ የሚረዱት ፡ ግልጽ ፡ የረቀቀና ፡ የተያያዘ ፡ አስተሳሰብ ፡ ያለው ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ ነው ። ይሁንና ፡ የሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ መጠናቀር ፡ ጉዳይ ፡ የተወሳሰበና ፡ ረቂቅ ፡ ችግሮችን ፡ ያዘለ ፡ ነው ። የኛም ፡ ዓላማ ፡ የሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ መጠናቀር ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለውን ፡ ኃይልና ፡ ገደብ ፡ ለማብራራት ፡ ያህል ፡ ሲሆን ፡ ወዲያውም ፡ የአዲሱን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ትክክለኛ ፡ ቦታና ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችለውን ፡ ግልጋሎት ፡ በተሻለ ፡ አኳኋን ፡ ለመረዳት ፡ ይጠቅም ፡ ይሆናል ።

በምዕራባውያን ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፤ ለምሳሌም ፡ በፈረንሣይና ፡ በጀርመን ፡ አገር ፤ ሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ የዋለበት ፡ ምክንያት ፡ ሕብረ ፡ ሰቦቹ ፡ ደርሰውበት ፡ ከነበረው ፡ የፖለቲካና ፡ የኤኮኖሚ ፡ አቋም ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ለመራመድ ፡ ተብሎ ፡ የጊዜው ፡ ታሪካዊ ፡ ሁኔታ ፡ የፈጠረው ፡ እርምጃ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ይቻላል ። ፈረንሣይና ፡ ጀርመን ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕግና ፡ የፍትሐ ፡ አሰጣጥ ፡ ዘዴ ፡ ከማግኘታቸው ፡ በፊት ፡ በፖለቲካና ፡ በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ ሲታዩ ፡ ታሪክን ፡ በሚመለከቱ ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሳ ፡ በየበኩላቸው ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ በመሆን ፡ ብሔራዊ ፡ አቋም ፡ ነበራቸው ። በእርግጥም ፡ ከአውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ በፖለቲካውና ፡ በኤኮኖሚው ፡ አቋምና ፡ በሕጉ ፡ አቋም ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ መራራቅ ፡ እስከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሳይጠብ ፡ ያልቀየው ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ነው ። በጊዜያችንም ፡ የሚገኝ ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ አቋም ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ጉድለት ፡ ማሟላት ፡ ሲያስፈልገውና ፡ የፖለቲካውም ፡ ሁናቴ ፡ የሚፈቅድ ፡ ከሆነ ፡ ምቹውና ፡ ፈጣኑ ፡ መንገድ ፡ ሕግ ፡ ማውጣቱ ፡ ነው ።

የሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ መውጣት ፡ ሌላው ፡ ዓላማ ፡ ደግሞ ፡ በተለይም ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ ሕብረ ፡ ሰቦች ፡ ዘንድ ፡ ጐልቶ ፡ የሚታየው ፡ ከዘመናዊ ፡ የሶሺያልና ፡ የኤኮኖሚ ፡ አቋም ፡ ጋር ፡ የማይስማሙትን ፡ አንዳንዶቹን ፡ የሶሺያልና ፡ የኤኮኖሚ ፡ ስልቶች ፡ የመቀየር ፡ ፍላጐት ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ ሁለት ፡ በጽሑፍ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ሊያበረክታቸው ፡ የሚችሉት ፡ ቁም ነገሮች ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ሕግ ፡ እንዲያውጁ ፡ ካነሳሷቸው ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ምክንያቶች ፡ መካከል ፡ ይገኛሉ ። እርግጥ ፡ የሕጉ ፡ መታወጅ ፡ ብቻውን ፡ ለነ ዚሁ ፡ ፍላጎቶች ፡ መሟላት ፡ ዋስትና ፡ አይሰጥም ። ቢጻፍም ፡ ባይጻፍም ፡ በአፈሴላዊ ፡ ሕግ ፡ እንዲሁም ፡ በአሠራርና ፡ በአስተሳሰብ ፡ መካከል ፡ ሰፊ ፡ ልዩነት ፡ አለ ። ለዚህም ፡ ጥሩ ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆነው ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ መጠሪያ ፡ ስም ፡ እንዲኖ ረው ፡ የሚያዘው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፪ ፡ ነው ።

ሕግን ፡ በተለይም ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈረን ፡ ሕግ ፡ በማወጅ ፡ አንድነት ፡ ያለውን ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ ለማግኘት ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዓይነቱ ፡ ሕብረ ፡ ሰብ ፡ ብዙ ፡ ችግሮች ፡ አሉበት ። ይሁንና ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ መነሻ ፡ ሌላ ፡ ስለሆነ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አናትትም ። ለአሁኑ ፡ ዓላማችን ፡ ሕግን ፡ በጽሑፍ ፡ ማስፈር ፡ አንድ ፡ ሕብረ ፡ ሰብ ፡ እንዲኖረው ፡ ለሚጥረው ፡ የሕግ ፡ አንድነትና ፡ ዘመናዊነት ፡ ተቀዳሚ ፡ ለሆኑት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሕጎችና ፡ መሠረተ ፡ ሃሳቦች ፡ መሠረት ፡ መጣል ፡ መሆኑን ፡ ማስታወስ ፡ በቂ ፡ ነው ።

እንግዳውስ ፡ በጽሑፍ ፡ የቀረበ ፡ ሕግ ፡ ለሌሎች ፡ ግቦች ፡ የሚሰጠውን ፡ አገልግ ሎት ፡ እንመልከት ። ከላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በመግቢያው ፡ ላይ ፡ በተለይ ፡ ሕጉ ፡ በቀላሉ ፡ የሚረዱት ፤ ግልጽ ፡ የሆነና ፡ የተያያዘ ፡ ሃሳብ ፡ ያለው ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ ገልጿል ። አንድ ፡ ሕግ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ፍላጎቶች ፡ በምን ፡ ዓይ ነትና ፡ እስከምንስ ፡ ደረጃ ፡ ነው ፡ ማሳካት ፡ የሚችለው? በጥንቃቄ ፡ የተዘጋጀ ፡ ሕግ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ቅደም ፡ ተከተልና ፡ ሕጉን ፡ ፈልጎ ፡ የማግኘት ፡ ዘዴ ፡ በማበርከት ፡ ለፍትሕ ፡ አሠራር ፡ ያገለግላል ። የተዋጣለት ፡ ሕግ ፡ በተራቀቀ ፡ መንገድ ፡ ሕጎችንና ፡ መሠረተ ፡ ሃሳቦችን ፡ ለማውጫ ፡ ያገለግላል ። እንዲሁም ፡ በፖሊሲያቸውም ፡ ሆነ ፡ በዓላማቸው ፡ ዝምድና ፡ ያላቸው ፡ እርእስተ ፡ ጉዳዮች ፡ ተቀራርበው ፡ ስለሚጻፉ ፡ ግን ኙነታቸውን ፡ በቀላሉ ፡ ማየትና ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ። ሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ ባልሰፈረበትም ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ አስቸጋሪም ፡ ቢሆን ፡ ቅሉ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆን ፡ ጥቅም ፡ የሚ ሰጡ ፡ የአሠራር ፡ ስልቶች ፡ አሉ ። ለምሳሌ ፡ በአሜሪካን ፡ አገር ፡ አፈሴላዊ ፡ ካልሆነው ፡ ከሕግ ፡ ራፖር ፡ ጋር ፡ በመቀነባበር ፡ የሚወጣውና ፡ በዝርዝር ፡ የሚሠራው ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፍርዶች ፡ ማውጫ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ለተመሠረተ ፡ ሕግ ፡ ውሳኔ ፡ መስጫ መምሪያ ፡ ይሆናል ።

በተጨማሪም ፡ በጽሑፍ ፡ የቀረበ ፡ ሕግ ፡ ለአንዳንድ ፡ ችግሮች ፡ የተረጋገጠ መልስ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ፤ በተለይም ፡ አንድ ዓይነት ፡ የሆኑ ፡ ወይም ፡ በጣም ፡ የሚመ ሳሰሉ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ እየተደጋገሙ ፡ ሲያጋጥሙ ፡ በዛ ፡ ያሉ ፡ አግባብ ፡ ያላቸውን ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታዎች ፡ በመመልከት ፡ መፍትሔአቸውን ፡ ለማግኘት ፡ ከመሻት ፡ ይልቅ ፡ በሕጉ ፡ በግልጽ ፡ የተደነገጉት ፡ መፍትሔዎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ ያስችላል ። ለምሳሌም ፡ ይህ ፡ የአካለ ፡ መጠን ፡ ዕድሜ ፡ በግልጽ ፡ ለመወ ሰን ፡ ሲያስችል ፡ «የውሉን ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማ ፡ ይነካል ፡ በማለት» ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ሺ፯፻፹፬ ፡ መሠረት ፡ ውሉን ፡ ለመሠረዝ ፡ እንዲቻል ፡ የውሉን ፡ አፈጻጸም ፡ የሚያግድ ፡ ሁናቴ ፡ በግልጽ ፡ ለመወሰን ፡ አያስችልም ። የተጻፍ ውም ፡ ሆነ ፡ ያልተጻፈው ፡ ሕግ ፡ በቀላሉ ፡ የሚረዱትና ፡ የማያጠራጥር ፡ የማይሆ ንበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ ተቀነባብሮ ፡ በጽሑፍ ፡ ያለውን ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ ያለ ምንም ፡ ሀሳብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ፈንታ ፡ ፍርድ ፡ ሰጪው ፡ ለትክክል ፡ ውሳኔ ፡ ሚዛናዊ ፡ አስተያየት ፡ እንዲኖረው ፡ በሚያስፈልግበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ሕግን ፡ ጠቀስ ፡ ደንቦች ፡ እንደሚታሰበው ፡ ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡ ቀላልና ፡ በማያጠራጥር ፡ አኳኋን ፡ ግልጽ ፡ ወይም ፡ ትክክል ፡ የሚሆኑበት ፡ ክፍል ፡ የኑሮ ፡ ፍልሥፍና ፡ ራሱ ፡

ለዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ አሠራር ፡ ተቃዋሚ ፡ በመሆኑና ፡ በሌሎችም ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሳ ፡ ከሚገመተው ፡ በላይ ፡ ጥቂትና ፡ ጠባብ ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ በጽሑፍ ፡ የሠፈሩ ፡ ሕጎች ፡ በተለይም ፡ በ፲፱ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ዕድለ ፡ ቢሱ ፡ የፕረሽያ ፡ ሕግ ፡ ይህን ፡ በተፈጥሮ ፡ ያለን ፡ የሕግን ፡ በጽሑፍ ፡ ማስፈር ፡ ገደብ ፡ ችላ ፡ ብለውት ፡ ነበር ። ብዙን ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ መሞከር፡ የግድ ፡ አደናጋሪና ፡ የማይሠራ ፡ ሁናቴን ፡ ያስከትላል ። ሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ ሲሰፍር ፡ ያለበት ፡ ገደብ ፡ በሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ ወይም ፡ ሕጉን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በሚያውሉት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በብዛት ፡ ሲዘነጋ ፡ የተጻፈው ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ረዥም ፡ ዕድሜ ፡ አይኖርውም ።

ሌላው ፡ መዘንጋት ፡ የሌለበት ፡ የሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ መውጣት ፡ ገደብ ፡ ደግሞ ፡ ጊዜው ፡ እየረዘመ ፡ ሲሄድ ፡ ለፍርድ ፡ አሰጣጥ ፡ ብቻውን ፡ በቂ ፡ መሆኑ ፡ እያነሰ ፡ መሄዱና ፡ በመጀመሪያ ፡ የነበረውን ፡ ቀላልነትና ፡ የተያያዘ ፡ ሃሳቡን ፡ እያጣ ፡ መሄዱ ፡ ነው ። የዚህም ፡ ምክንያት ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ጊዜው ፡ እየረዘመ ፡ ሲሄድ ፡ ሕጉ ፡ በቅድሚያ ፡ ያላሰበባቸውና ፡ እንዲያውም ፡ ሊያስብባቸውም ፡ የማይቻሉት ፡ አዳዲስ ፡ ችግሮችና ፡ አስተሳሰቦች ፡ ሲመጡ ፡ ከሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የማይገኙ ፡ አዳዲስ ፡ መፍትሄዎች ፡ አስፈላጊ ፡ ይሆናሉ ። በተጨማሪም ፡ በሕጉ ፡ አንቀጾች ፡ በመጠቀም ፡ የፍርድ ፡ አሰጣጥ ፡ ልምምድ እየጨመረ ፡ ሲሄድ ፡ ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውል ፡ የሚሰጠውን ፡ ትርጉም ፡ ለመረዳት ፡ መታወቅ ፡ ያለባቸው ፡ ነገሮች ፡ እየበዙ ፡ ይሄዳሉ ። እንዲሁም ፡ ሕጉ ፡ እየጐለመሰ ፡ በሚራመድበት ፡ ጊዜ ፡ የሕጉም ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ እየመነመነ ፡ በመጨረሻም ፡ ለፎርማሊቲ ፡ ያህል ፡ ለሕግ ፡ አስተሳሰብ ፡ ትንተና ፡ መነሻ ፡ በማገልገል ፡ መግለጫቸው ፡ እየታተሙ ፡ እንደሚወጡ ፡ ጽሑፎች ፡ ምቹ ፡ የሕግ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ኖሮት ፡ ሕጉን ፡ በቀላሉ ፡ ለማግኘት ፡ ብቻ ፡ ከሚያገለግልበት ፡ ደረጃ ፡ ይደርሳል ። እንደ ፡ አውሮፓ ፡ አቆጣጠር ፡ በ፲፰፻፬ ፡ ዓ. ም. የወጣው ፡ የፈረንሣይ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአንዳንድ በኩል ፤ ለምሳሌ ፡ በቀላል ፡ ጥፋቶች ፡ ጉዳይ ፤ እዚህ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ደርሷል ።

ቀደም ፡ ተብሎ ፡ የሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ መዋል ፡ ከሚያስገኘው ፡ ጥቅም ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ የተጠቀሱት ፡ ሕጉ ፡ በቀላሉ ፡ የሚገባ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽነቱና ፡ የተያያዘ ፡ ሃሳብ ፡ መያዙ ፡ የሚያስከትሉትም ፡ ገደብ ፡ አለ ። በሕጉ ፡ ጮርቃነት ፡ ዘመን ፡ ሊያስፈጽም ፡ ከሚችለው ፡ በላይ ፡ ያስፈጽማል ፡ ብሎ ፡ የመገመት ፡ የሰው ፡ ዝንባሌ ፡ በመኖሩ ፡ ይሀ ፡ የሕግ ፡ አተርጓጐም ፡ በዘልማድ ፡ በደረቁ ፡ እንዲሆን ፡ በማድረጉ ፡ የሕግን ፡ ዕድገት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ይጐትታል ። በጽሑፍ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ችግሮች ፡ በምናስብበት ፡ ጊዜ ፡ ይረዳናል ፡ እንጂ ፡ ማሰብንና ፡ ማመዛዘንን ፡ መተካት ፡ የለበትም ።

ሕግን ፡ በጽሑፍ ፡ ስለማውጣት ፡ በምናስብበት ፡ ጊዜ ፡ ለሕግ ፡ ነክ ፡ ችግሮች ፡ ትክክለኛ ፡ መፍትሔ ፡ የሚገኘው ፡ በሕጉ ፡ ጠቅላላ ፡ አቋምና ፡ የተቀነባበረ ፡ ሃሳብ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ የያዘውን ፡ ዕውነተኛ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በመመልከት ፡ መሆኑንም ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ። ሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ በሰፈረበት ፡ የሕግ ፡ አመራር ፡ ዘዴ ፡ በተለይም ፡ ደግሞ ፡ ሕጉ ፡ ከወጣ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ካልሆነው ፡ በአብዛኛው ፡ ክፍል ፡ ምናልባትም ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ በአጠቃላይ ፡ መንገድ ፡ ለመሥራት ፡ ይሞከራል ። (በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ ባልሠፈረበት ፡ የሕግ ፡ አመራር ፡ ዘዴ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ እያንዳንዱን ፡ ጉዳይ ፡ አትኩሮ ፡ የሚመለከት ፡ ይሆንና ፡ የአቋሙና ፡ የተያያዘ ፡ ሃሳቡ ፤ የአመዳደብና ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ማስጠበቅ ፡ ኃይሉ ፡ እየጠፋ ፡ ይሄድ ፡ ይሆናል) ። ስለዚህ ፡ በጽሑፍ ፡ የሠፈረ ፡ የሕግ ፡ አመራር ፡ ዘዴ ፡ በሕጉ ፡ በመጠቀም ፡ የተሰጡትን ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔዎች ፡ በማጥናት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ይሰጣል ። የዚህ ፡ ዓይነቱም ፡ ጥናት ፡ የአንድ ፡ ልዩ ፡ ችግር ፡ ዕው

ነተኛና ፡ ዝርዝር ፡ ሐተታዎች ፡ መታወቅ ፡ እንዳለባቸው ፡ የሕጉን ፡ ሊቅ ፡ ያሳስባል ።
(በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በጽሑፍ ፡ ያልዋለው ፡ የሕግ ፡ አመራር ፡ ዘዴ ፡ ለየክርክሩ ፡
በተሰጡት ፡ ልዩ ፡ ውሳኔዎች ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ የሊቃውንት ፡ ጽሑፍ ፡ በሚሰጠው
አቋምና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሊጠቅም ፡ ይችላል) ።

የሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ መዋል ፡ ያለውን ፡ አንዳንድ ፡ ኃይል ፡ ወይም ፡ ገደቦች ፡ ስና
ወሳ ፡ ዋናው ፡ ዓላማችን ፡ የተጻፈውም ፡ ሆነ ፡ ያልተጻፈው ፡ የሕግ ፡ አመራር ፡ ዘዴ ፡
የተሟሉን ፡ ዘላቂ ፡ የሆኑ ፡ መፍትሄዎችን ፡ እንደማይሰጥ ፡ ለማሳየት ፡ ነው ። አንዳንድ ፡
በጽሑፍ ፡ የዋሉ ፡ የሕግ ፡ አመራር ፡ ዘዴዎች ፡ በትክክለኛ ፡ አነጋገር ፡ የተሟሉ ፡
ናቸው ፡ እየተባለ ፡ በፊት ፡ ጊዜ ፡ ይነገር ፡ ነበር ። ይህም ፡ ማለት ፡ የሕጉ ፡ አመራር
ዘዴ ፡ ለማንኛውም ፡ ችግር ፡ መፍትሔውን ፡ በግልጽ ፡ ሰጥቷል ፤ ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ደግሞ ፡
የፖሊሲንና ፡ የሕሊናን ፡ ዋጋ ፡ ጉዳይ ፡ በማይመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ከተጻፈው
ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ፍጹም ፡ ቀጥተኛ ፡ በሆነና ፡ ቀደም ፡ ተከተል ፡ ባላቸው ፡ የአስተሳሰብ ፡
ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ አማካይነት ፡ መፍትሄውን ፡ ማግኘት ፡ ይቻላል ፡ ማለት ፡ ነው ።
ይህ ፡ ቀጥተኛ ፡ በሆነና ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ባለው ፡ የአስተሳሰብ ፡ ዘይቤ ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡
የተሟላ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ የሚለው ፡ የድፍረት ፡ አነጋገር ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ የተ
ነገረለትን ፡ ውጤት ፡ ሳያሳይ ፡ ቀርቷል ። ለፍርድ ፡ ችግር ፡ መፍትሄ ፡ መፈለጊያ ፡ አድ
ርገን ፡ እርምጃ ፡ የምንጀምርባቸው ፡ የሕግ ፡ መመሪያዎች ፡ (በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡
የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሆኑ ፡ ነው) ፡ በእርግጥ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ደረጃ ፡ የተዘጋጁና ፡
ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ የተከተሉ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ የኑሮ ፡ ልምድ ፡ የያዙ ፡ ናቸው ። ትክክ
ለኛ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ አመራር ፡ ለሕጋዊ ፡ አስተሳሰብ ፡ መመሪያና ፡ መነሻ ፡ ይሆኑ ፡
ዘንድ ፡ የተደነገጉትን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶችና ፡ መመሪያዎች ፡ ሲቀበል ፡ የጊዜው ፡ ሁና
ቴና ፡ የሕሊና ፡ ዋጋም ፡ ሲለወጥ ፡ አዳዲስ ፡ መፍትሄዎች ፡ አስፈላጊ ፡ ሊሆኑ ፡ እንደሚ
ችሉ ፡ በመገንዘብ ፡ ነው ። የሕጉ ፡ ሊቅ ፡ ኃላፊነት ፡ የፊተኞቹ ፡ መፍትሄዎች ፡ ትክክል ፡
ሆነው ፡ በማይታዩበት ፡ ጊዜ ፡ ከኅብረ ፡ ሰቡ ፡ ፍላጎትና ፡ ልምድ ፡ ጋር ፡ የሚስማሙ ፡
አዳዲስ ፡ መፍትሄዎች ፡ መፍጠር ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በጽሑፍ ፡ የቃልን ፡ ሕግ ፡ መረዳት ፡ ሰዋስውን ፡ ወይም ፡ መዝገበ ፡ ቃላ
ትን ፡ እንደ ፡ መረዳት ፡ አድርጋችሁ ፡ የገመታችሁ ፡ እንደሆነ ፡ የወደፊቱ ፡ የሕግ ፡ ሊቃ
ውንት ፡ እንደመሆናችሁ ፡ መጠን ፡ ለዘለቄታው ፡ ሥራችሁና ፡ ለአገራችሁም ፡ በደል ፡
ይሆናል ። ስለሕጉ ፡ እንቀጾች ፡ የተሰጠውን ፡ የፖሊሲ ፡ መመሪያ ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊ ፡
ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የሕጉ ፡ አርቃቂዎች ፡ እንኳን ፡ ወደፊት ፡ ምን ፡ እንደሚያስፈልግ ፡
በሙሉ ፡ ማወቁ ፡ ቀርቶ ፡ ሕጉ ፡ በሚረቅበት ፡ ጊዜ ፡ ያሉትን ፡ የተወሳሰቡ ፡ ረቂቅ ፡
ጉዳዮች ፡ በሙሉ ፡ አጠናቀው ፡ ሊያውቁ ፡ እንዳልቻሉ ፡ ማስታወስ ፡ ያስፈልጋል ።
ይህን ፡ ካስታወሳችሁ ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ እንደመሆናችሁ ፡ መጠን ፡ ሕጉን ፡ በማደ
ርጀትና ፡ ሕብረ ፡ ሰቡም ፡ ሕጉ ፡ በተነደፈበት ፡ ጊዜ ፡ ሊገመቱ ፡ ያልተቻሉና ፡ አሁን ፡
የተፈጠሩትን ፡ አዲስ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ለመረዳት ፡ በሚችልበት ፡ ጊዜ ፡
ኃላፊነታችሁን ፡ ገሸሽ ፡ ታደርጋላችሁ ፡ የማለቱ ፡ ዕድል ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ይሆናል ።